**ORAC SP/02**

# Oifig an Choimisinéara Iarratais do Dhídeanaithe

## የስደተኛ ማመልከቻዎች ኮሚሽንነር ቢሮ

**<u>የአወሮፓ ህብረት (የተደጓሚ ጥበቃ) ደንቦች፣ 2013 (S.I.No 426 በ2013)</u>**

ለአመልካቾች ተደጓሚ ጥበቃ የምርመራ እና ውሳኔ አካሂዶች

ለአመልካቾች የመረጃ ማስታወሻ

ይኸ ማስታወሻ ለመረጃ እና መምሪያ ብቻ ነው፡፡ የእነዚህን ደንቦች የህግ ትርጓሜ ፍች አይሰጥም፡፡

## 1. መግቢያ

1.1. ይኸ የመረጃ ማስታወሻ ለተደጓሚ ጥበቃ ምርመራ እና ውሣኔ ላይ ያለውን ገዥ ህግ ዝርዝር ያቀርባል፣ በአወሮፓ ህብረት /የተደጓሚ ጥበቃ/ ለተከተሉ መንግስታት ደንቦች 2013 /s.t. No 426 በ2013/ (”የ2013 ደንቦች)

1.2. የ2013 ደንቦች የተደነገጉት በፍትህ እና እኩልነት ሚኒስተር (”ሚኒስተር”) እናም የተገበረው በኖቬምበር 14፣ 2013 (”የተጀመረበት ቀን”) ነው፡፡

1.3. በ2013 ደንቦች የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻዎች የስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር /”ኮሚሽነር”/ ኋላፊነት ሆኗል፡፡

1.4. <u>በሌሎች ነገሮች መሃል መረዳታችሁን ለማረጋገጥ ይህን የመረጃ ማስታወሻ በጥንቃቄ ማንበብ አሰፈላጊ እና ለእናንተም የሚጠቅም ነው፡-</u>

i. ለተደጓሚ ጥበቃ የመጨረሻውን የማመልከቻችሁን ውሳኔ እየጠበቃችሁ በአየርላንድ ውስጥ መብታችሁ፣ ግዴታችሁ እና ኋላፊነታችሁ፡፡

ii. የ2013 ደንቦች አካሄዶች የእርስዎ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ሂደት ጋር በተዛመደ ይካሄዳል፡፡

iii. በ2013 ደንቦች የተቀመጡትን የጊዜ ገደቦችን እና ሌሎች መስፈርቶች ትዕዛዝ መቀበል እና ለእያንዳዱ ሂደት ደረጃ ላይ በፍጥነት መመለስ፡፡

1.5. ስለ ደንቦች ለእያንዳንዱ ባለ ጉዳይ እንደ ሚተገበሩ የበለጠ መረጃ ከአስፈለገዎ የህግ ምክር ማግኘት ይገባዎታል፡፡

2. የ2013 ደነቦች ዓላማ

2.1. እነዚህ ደንቦች ለአዲስ የተደጓሚ ጥበቃ ምርመራ እና ውሳኔ በኖቬምበር 14 እና በፊት በየመንግስታቱ የተሰጡትን ስርዓት ይሰጣል፡፡

2.2. በፍትህ እና እኩልነት ሚኒስተር የአይሪሽ የዜግነት መብት አሰጣጥ እና የስደተኞች አገልግሎት ነባር ተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻዎችም ያገለግላሉ፣ የ2013 ደንቦች ከተጀመሩበት ቀን በፊት ያልተወሰኑ እና ከዛን ቀን ጀምሮ በኮሚሽኑ የተላለፉ ፡፡

**3. የ2013 ደንቦች ምን ይሸፍናሉ?**

**ለተደጓሚ ጥበቃ አዲስ አመልካች ከሆኑ**

3.1. በ2013 ደንቦች ኖቨምበር 14፣ 2013 ጀምሮ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻዎች የሚመረመሩበት እና የሚወሰኑት በኮሚሽኑ መሆኑን ያቀርባል፡፡

3.2. ከዚህ ቀን ጀምሮ ለተደጓሚ ጥበቃ አዲስ ማመልከቻዎች ለፍትህ እና እኩልነት ሚኒስተር ሊደረጉ ይችላሉ ነገር ግን በተገቢው ማመልከቻ ቅፅ ለኮሚሽኑ የቀረቡ መሆን አለባቸው፡፡ ለኮሚሽኑ በ2013 ደንቦች መሰረት እና የተደጓሚ ጥበቃ አመልካቹን ቃለ መጠይቁን በመከተል የፅሑፍ ዘገባ ያቀርባል፡፡ ኮሚሽኑ ለፍትህ እና እኩልነት ሚኒስተር አመልካቹ የተደጓሚ ጥበቃ የሚገባው ሰው መሆኑን እና አለመሆኑን ምስክርነት ይሰጣል፡፡

**ማመልከቻው በሚኒስተሩ ያልተወሰነ የተደጓሚ ጥበቃ ነባር አመልካች ከሆኑ:-**

3.3. የ2013 ደንቦች ከመጀመራቸው በፊት በፍትህ እና እኩልነት ሚኒስተር ያልተወሰኑ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻዎች ለምርመራ እና ውሳኔ ለኮሚሽኑ ተላልፋዎል፡፡ ሚኒስትሩ እነዚህን ሁሉንም አመልካቾች ሰለ አዲስ የእነርሱን ማመልከቻ አካሄድ እሳቤ ያሳውቃል፡፡

3.4. እንዲህ አይነት ሰው ለኮሚሽኑ አዲስ ማመልከቻ ማቅረብ አይጠበቅበትም ነገር ግን ማጠናከሪያ ማስገባት ይኖርበታል (ከታች ያለውን አንቀፅ 7.5 ይመልከቱ)።

**4. የተደጓሚ ጥበቃ ምንድን ነው?**

4.1. ተደጓሚ ጥበቃ ጥበቃ ሆኖ የሚሰጠው አንድ ሰው ወደ ትውልድ ሀገሩ ቢመለስ ከፍተኛ ስቃይ እና ጉዳት ሊደርስበት ወይም መቋቋም የማይችልበት በቂ መሰረት መኖሩ ከታመነበት ነው፡፡ የዛ ሀገር ጥበቃ ሥር ለመሆን ፍቃደኛ ያልሆነ ከሆነ እና ለተደጓሚ ጥበቃ ከተገቢነት ያልወጣ ሲሆን ነው፡፡

4.2. <u>ከባድ ጉዳት</u> ማለት

ሀ/ የሞት ቅጣት ወይም የሞት ፍርድ ወይም

ለ/ በትውልድ ሀገር ውስጥ በድብደባ ማስቃየት ወይም ሰብዓዊ ያልሆነ ወይም አዋራጅ አየያዝ ወይም ቅጣት ወይም

ሐ/ ከባድ እና ወታደር ያልሆኑ ግለሰቦች የህይወት ስጋት ወይም ሰው ከሰው ያልለየ አረብሻ ምክንያት፡፡

4.3. ለተደጓሚ ጥበቃ ብቁ ከሆኑ በሀገሩ እንዲቆዩ ይፈቀድለዎታል እናም የተወሰኑ መብቶች እና ፈቃዶች ብቁ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ መብቶች እና ፈቃዶች በ2013 ደንቦች ውስጥ ቀርበዋል፡፡

## 5. ለተደጓሚ ጥበቃ ብቁ የሚሆነው ማን ነው?

5.1. ማመልከቻውን ሲያደርጉ ያሉት በዛ ሀገር ውስጥ ሆነው ነው ብንል፣ በ2013 ደንቦች መሰረት እርስዎ የተደጓሚ ጥበቃ የሚያገኙት፡-

ሀ/ የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ዜጋ ካልሆኑ፡፡

ለ/ በአየርላንድ ውስጥ አንደ ስደተኛ ተቀባይነት ካላገኙ

ሐ/ ወደ ትውልድ ሀገሩዎ ቢመለሱ ከባድ ጉዳት ስቃይ የሚጠብቅዎ ወይም እነዚህ ስጋቶች ሰለሚደርስብዎ ለዛ ሀገር ጥበቃ እራስዎን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆነው በበቂ መሰረት ከታየ እና

መ/ ተገቢ /ብቁ/ አይደሉም ካልተባሉ

5.2. በ2013 ደንቦች መሰረት ፡ ከተደጓሚ ጥበቃ ብቁ ከመባል ሊወገዱ የሚችሉት -

ሀ/ ሰላምን የሚነሳ ወንጀል ፈፅመዋል፡ የጦር ወንጀል ፡ በሰው ልጆች ላይ ወንጀል በአለም አቀፍ መሣሪያዎች ላይ እንደተቀመጠው እነዚህን ወንጀሎች፡

ለ/ ከባድ ወንጀል ከፈፀምክ/ሽ፡-

ሐ/ ከበተባበሩት መንግስታት እና መርሆች ተፃራሪ ድርጊቶችን በተባበሩት መንግስታት የቻርተሩ መግቢያ አንቀፅ 1 እና 2 ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ወይም

መ/ ለማህበረሰቡ አደጋ ወይም ለሀገር ስጋት ከሆኑ

5.3. ከተደጓሚ ጥበቃ ብቁነት ሊወገዱ የሚችሉት ደግሞ፡-

i. ወንጀልን በማነሳሳት ወይም ወንጀል እንዲሰራ በማስተባበር ከተሳተፉ ወይም በአንቀፅ 5.2. ከ(ሀ) እስከ (መ) የተጠቀሱትን ድርጊቶች
ii. ከወንጀል ወይም ወንጀሎች የትውልድ ሀገረዎን ጥለው የመጡት በወልጀንና ወንጀል ምክንያት ከተጣለው ማእቀብ ለማምለጥ (ነገር ግን በአንቀፅ 5.2 ሀ እሰከ መ ድረስ ወንጀል ወይም ባህሪይ ያልተካተተ) በዚህ ሀገር እነዚህ ድርጊቶች ተፈፅመው ቢሆን በእስራት የሚያስቀጡ ሆነው እዚህ ሀገር ከመግባቶዎ በፊት የፈፀሙት ከሆነ፡፡

## 6. በዚህ ሀገር ለተደጓሚ ጥበቃ ማን ሊያመለክት ይችላል?

6.1. በ2013 ደንቦች የተደጓሚ ጥበቃ በአንድ ሰው ሊደረግ የሚችለው

ሀ/ በዚሁ ሀገር ውስጥ ላሉ እና

ለ/ አየርላንድ ውስጥ እንደ ስደተኛ ተቀባይነት ያላገኙ

6.2. ሚኒስተሩ የስደተኛነት ህጋዊ ሰነድ ላለመስጠት ከወሰነ የእርስዎ የስደተኛነት ህጋዊ ሰነድ ማመልከቻ ያልተፈቀደ መሆኑን ማስታወቂያው ይላክሎዎታል፡፡

6.3. ማስታወቂያው ስለ ተደጓሚ ጥበቃ እና ማመልከከቻ ቅፅ የመረጃ ማስታወሻ ይኖረዋል፡፡ተደጓሚ ጥበቃ ይገባኛል ብለው የሚያስቡ ከሆኑ ማስታወቂያው ከተላከበት ጀምሮ ባሉት 15 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅፁን ሞልተው ለኮሚሽነሩ መመለስ አለቦት፡፡

## 7. በስደተኞች ማመልከቻዎች ኮሚሽነር የኄ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ እንዴት ይመረመራል?

7.1. የእርስዎ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ኮሚሽነሩ የሚመረመረው እና የሚወሰነው በ2013 ደንቦች መሠረት ነው፡፡

7.2. ለአዲሱ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻዎት አካሄድ ሂደት ማመልከቻዎን በተመለከተ ለቃለ መጠይቅ መገኘት ይጠበቅብዎታል፡፡ የቃለ መጠይቁ አላማ የተደጓሚ ጥበቃ አቢቱታ ሙሉ ዝርዝር የሚመሰረትበት ነው፡፡

7.3. አመልካች በስደተኞች ማመልከቻዎች ኮሚሽነር ቢሮ ለቃለመጠይቅ መገኘት አለበት፡፡ አመልካቹ በተየዘላቸው ቀጠሮ ቀን ካልቀረቡ የእርሱ ወይም የእርሷ ማመልከቻ ሊወጣ እንደሚችል ይታሰባል፡፡ /አንቀፅ 8.2ን ይመልከቱ/

7.4. <u>አመልካች ለምርመራው ማንንም የሚጠቅም ነገር ጋር በተዛመደ ለኮሚሽነሩ አመልካቹ በውክልና ገለፃ ይችላል እናም ኮማሽነሩ ከቃለ መጠይቁ በፊትም ሆነ በቃለ መጠይቁ ጊዜ የተደረጉትን ማንኛውም ውክልናዎች በ2013 ደንቦች መሰረት አመክሮ ውስጥ ያስገባል፡፡ የፅሑፍ ውክልናዎች በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካሚሽንም ሆነ ማንኛውም ጉደዩ የሚመለከተው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡</u>

7.5. የ2013 ደንቦች በተጀመሩበት ጊዜ ማመልከቻዎ ያልተወሰነ ነባር የተደጓሚ ጥበቃ አመልካች ከሆኑ በአይሪሽ የዜግነት ሙብት እና አስጣጥ አገልግሎት ተጨማሪ ገለፃዎችን ሰነዶችን ጨምሮ ከኮሚሽነሩ የተላከለዎን የመመሪያ ሰነድ እና እንዲሁም ደብዳቤ እንዲያማከሩ ይጠየቃሉ፡፡

7.6. አግባብ ያለው መግባባትን በቃለ መጠይቁ ጊዜ ለማረጋገጥ ሲባል አሰፈላጊ ሲሆን ኮማሽነሩ አስተርጓሚ ያቀርባል፡፡

**የሂደቱ አካሄዶች ዋና ገፅታ**

7.7. የተደጓሚ ማመልከቻዎች ሂደት አካሄዶች ዋና ገፅታዎች እንደሚከተለው ነው፡-

i. ከእርስዎ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ ለቃለ መጠይቅ እንዲቀርቡ ኮሚሽነሩ ያዘጋጃል፡፡
ii. ቃለ መጠይቁን ተከትሎ፣ በእርስዎ ማመልከቻ ምርመራ ውጤት ላይ የፅሑፍ ዘገባ ይዘጋጃል እናም በኮሚሽነሩ እርስዎ ለተደጓሚ ጥበቃ ብቁ ይሁኑ አይሁኑ የተሰጠውን ዋቢነት ለፍትህ እና እኩልነት ሚኒስተር ያዘጋጃል፡፡
iii. መጥፎ ዋቢነት ወይም አስተያየት በሚሆንበት ጊዜ ለስደተኛ ይግባኝ ልዩ ፍርድ ቤት / "ልዮ ፍርድ ቤት"/ በኮሚሽነሩ መጥፎ ዋቢነት ማስታወቂያ በደረሰው 15 የሥራ ቀናት ውስጥ በአስተያየቱ ይግባኝ እንዲጠይቁ ይፈቀድለታል፡፡ ልዩ ፍርድ ቤት በንግግር ችሎት ያካሄዳል: አመልካቹ ይኽን የእርሱን /እርሷን/ ይግባኝ ማስታወቂያ ይጠይቃል፣ አልያም ይግባኝ ያለቃል ንግግር ሊወሰን ይችላል፡፡
iv. በኮሚሽነሩ ምስክርነት ወይም አስተያየት መሰረት ወይም በልዩ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሚኒስትሩ በ2013 ደንዶች መሰረት የተደጓሚ ጥበቃ መብት እንደ አግባብነቱ ለእርስዎ ሊሰጠም ላይሰጥም ይችላል፡፡

7.8. በሚኒስትሩ የእርስዎ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ካልተቀበለው የሚከተለውን የሚገልፅ ይላክለዎታል፡-

ሀ/ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻዎ ተቀባይነት አላገኘም

ለ/ በሀገሪቱ እንዲቆዩ የተፈቀደለዎ ጊዜ አልፏል፡፡

ሐ/ ሚኒስትሩ በስደተኛ ድንጋጌ 1999 ክፍል 3 መሰረት ሀገር ለቀው እንዲወጡ እንደሚገባዎ ሚኒስተሩ እንደወገዱ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

መ/ ገለፃዎችን ወይም አቢቱታዎችን በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለምን በሀገሪቱ ውስጥ እንዲቆዩ ሊፈቀድለት እንደሚገባ አዘጋጅተው ማቅረብ አለበዎት፡፡

## 8. አስፈላጊ፡- የኔን የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ማንሳት እችላለሁ ወይም ማመልከቻው እንደተነሳ ይታሰባል?

8.1. አመልካቹ የእርሱን ወይም የእርሧን የተደጓማ ጥበቃ ማመልከቻ የማንሻ ማስተወቂያ ለኮማሽነሩ በመላክ ማንሳት ይቻላል፡፡

8.2. አመልካቹ በተያዘለት ቀጠሮ ለቃለ መጠይቅ ጊዜ በኮሚሽነሩ ካልተገኙ፣ አመልካች ከዛ ቀን ከ3 የስራ ቀናት ባለለፈ ለኮሚሽነሩ ያልተገኘበትን ምክንያት ለኮሚሽነሩ ገለፃ ካላቀረበ በኮሚሽነሩ ሀሳብ የሁኔታዎችን ምክንያታዊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር የእርሱ ወይም የእርሷ ማመልከቻ በ2013 ደንቦች መሰረት ይነሳል፡፡

8.3. ለኮሚሽነሩ አመልካች እንዲህ መስሎ ከታየው፡-

(i) አመልካች ኮሚሽነሩ በማመልከቻው ላይ የሚያደርገውን ምርመራ ካልተባበሩ ወይም

(ii) ለተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ጠቃሚ መረጃ ለመስጠት የእርሱ ወይም የእርሱ ሀላፊነት ካጓደሉ ወይም

ሚኒስትሩ ለኮሚሽነሩ እርሱ ወይም እርሷ ሀላፊነታቸውን አጉድለዋል የሚል ሀሳብ ሲል

(iii) ያለ ሚኒስትሩ ፈቃድ ሀገሪቱን ላለመልቀቅ ወይም ለቆ ለመሄድ መሞከር

(iv) ለኮሚሽነሩ የእርሱ ወይም የእርሷን አድራሻ ወይም የአድራሻ ለውጥ ወዲያውኑ በተቻለው ፍጥነት አለማሳወቅ፡፡

ኮሚሽነሩ የፅሁፍ ማሳወቂያ መላክ ይኖርበታል፤ ማሳወቂያው በተላከ ባሉት 15 የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን እርሱ ወይም እርሷ የመቀጠል ፍላጎት እንዳላቸው ይጋብዛል፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ገደብ የማመልከቻው ህጋዊ ሰነድ በ2013 ደንቦች መሰረት ይነሳል፡፡ በእንደዚህ አይነት ማመልከቻ የኮሚሽነሩ ዘገባ ሰውዬው ለተደጓሚ ጥበቃ ብቁ አለመሆኑን የሚያሳውቅ አስተያየት ወይም ዋቢነት ማከል አለበት፡፡

8.4. ለተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ከተነሳ ወይም ሊነሳ የታሰበ ከሆነ ለስደተኞች ልዩ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም፡፡

## 9. የተደጓሚ ጥበቃ ሂደትን በተመለከተ የመረጃ አቅርቦት

9.1 የ2013 ደንቦች በሙሉ በስደተኛ ማመልከቻዎች ኮሚሽነሩ ድህረ ገፅ at http://www.ORAC.ie. ማግኘት ይችላሉ፡፡

9.2 ይኸ የመረጃ ማስታወሻ በስደተኛ ማመልከቻዎች ኮሚሽነር ድህረ ገፅ ላይ በብዙ ቋንቋዎች ይገኛል፡፡

## 10. ሌላ መረጃ

10.1 ጥበቃ የመጠየቅ መብት አለዎት እናም ከእርስዎ የተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ የስድስተኛ የህግ አገልግሎት (RLS) መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የስድስተኛ የህግ አገልግሎት /RLS በአየርላንድ ውስጥ ለጥበቃ የሚያመለክቱ ሰዎችን ሚስጥራዊ የህግ አገልግሎት ለማቅረብ የተመሰረተ ራሱን የቻለ አካል ነው፡፡ የእርስዎን ማመልከቻ በመደገፍ የስድስተኛ የህግ አገልግሎት/RLS የህግ ምክር እና እገዛ ያደርጋል፡፡ እንደ አማራጭም፣ በእራስዋ ወጭ የግል ጠበቃ መፈለግ ይችላሉ፡፡ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነርንም የማማከር መብትም አለ፡፡

10.2 ከተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚደረግ ድረስ በሀገር ውስጥ የመቆየት ፈቃድ አለዎት ፡፡ ሚኒስትሩ ለነባር አመልካቾች የዚህን ውጤት አስመልክቶ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡ አዲስ አመልካቾች ይኸን ደብዳቤ ከኮሚሽነሩ ይቀበላሉ፡፡

10.3 በዚህ የመረጃ ማስታወሻ ያልተካተቱ ለአካሄድ ጉዳዮች እና ለተደጓሚ ጥበቃ ብቁ የሆነን ሰው የተሰጠውን ስልጣን እና መብቶች ዝርዝር እና የዋለውን የተደጓሚ ጥበቃ ህጋዊ ሰነድ ጋር በተያያዘ የ2013 ደንቦች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

**በተጀመረበት ቀን በሚኒስትሩ ላልተወሰነባቸው ነባር አመልካቾች ተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻዎች**

10.4 በ2013 ደንቦች በተጀመረበት ጊዜ፣ለተደጓሚ ጥበቃ ማመልከቻ ከአቀረቡ እና በማመልከቻው ላይ እስካሁን ያልተወሰነለዎት ከሆነ የሚከተለውን ያስተውሉ፡-

ኮሚሽነሩ የቃለ መጠይቁን ዝግጅት በተመለከተ በሂደት ያገኙታል ስለዚህ የስደተኛ ማመልከቻዎች ኮሚሽነር ቢሮ/ORAC በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማግኘት አያስፈልግዎትም

- የተደጋጋሚ ጥበቃ ማመልከቻ እየተመረመረ እያለ ምንም አይነት ከሀገር የመባረር ስጋት/አደጋ ውስጥ አደሉም/ አይሆኑም

**ኖቬምበር 14/2013**

## አንዳንድ ጠቃሚ አድራሻዎች

**የስደተኛ ማመልከቻዎች ኮሚሽነር ቢሮ**
ቲምበርሊ ሃውስ,
79-83 ሎወር ማውንት ስትሪት,
ደብሊን 2.
ስልክ: 01 6028000
የአካበቢ ቁጥር: 1890 202 418
ድህረገጽ: www.orac.ie
ኢሜል: oracmail@orac.ie

**የይግባኝ ልዮ ፍርድ ቤት**
ሃኖቨር ስትሪት ኢስት,
ደብሊን 2.
ስልክ: 01 4748400
የአካበቢ ቁጥር: 1890 201 458
ድህረገጽ: www.refappeal.ie
ኢሜል: info@refappeal.ie

**የስደተኛ የህግ አገልግሎት**
ሪፉጂ ሊጋል ሰርቪስ ሎው ሴንተር፡ ስሚዝፊልድ,
48/49 ኖርዝ ብሩንስዊክ ስትሪት,
ጆርጅስ ሌን,
ደብሊን 7.
ስልክ: 01 646 9600.
ድህረገጽ: www.legalaidboard.ie
ኢሜል: lawcentresmithfield@legalaidboard.ie

**አለም አቀፍ የስደተኞች ደርጅቶች**
116 ሎወር ባጎት ስትሪት,
ደብሊን 2.
ነጻ ስልክ: 1800 406 406
ስልክ: 01 6760655
ድህረገጽ: www.ireland.iom.int
ኢሜል: iomdublin@iom.int

**የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽነር**
ሱት 4,
ሜሪዮን ሃውስ,
1-3 ሎወር ፊዝዊሊያም ስትሪት, ደብሊን 2.
ስልክ: 01 6314510.
ድህረገጽ: www.unhcr.ie.
ኢሜል: iredu@unhcr.org.